#3

## አ"ፍሪ"ድዋ /አ"Free"ድዋ/ (አፍሪካ+አድዋ)

የጥቁር አንፀባራቂነት አስኪገለጥላቸው እንደ ፋና
ብዙ ጊዜያትን ፈጅቶ ነበር ከተመልካቾቹ ስንፍና
ሲፈልጉት ስለቆዩ ከተሳሳተ ጎዳና፡፡
እስከ 1888 የኢትዮጵያን አፈር እስኪደፍሩት
ጥቁር ሁሉ እቃ ነበር እንዳሻቸው የሚገዙት፤
እንዳሻቸው የሚሸጡት፡፡
ጣሊያን የተሸነፈው
ገና ዱሮ ነው በጦርነቱ ሳይረታ
ግልጥ መናገሩን ፈርቶ
የውጪ ትርጉሙን ሲያምታታ፡፡
እናም በተሸነፈ ወኔያቸው
በለመደ እግራቸው በህልም አለም ቅዠታቸው
ኢትዮጵያን ሊገዙ ሲመጡ ምኒልክ ምን ብሎ መለሳቸው?
‹‹በርካሽ የዛገ ሀሳብ በተወለወለ የብረት ጠብመንጃ
ትጠቀምበት ይሆናል እንጂ ለግጦሽህ ከብትን ማገጃ
ምን ቀን ቢዞርብህ? ምን መካሪ ቢያሳጣህ?
ድሪቶህን ሸክፈህ ጥቁር አልማዝ አምሮህ መጣህ?
በል ዞር በልልኝ ከፊቴ ቁጣዬን በግድ አትቀስቅሰው
በአንዲት ሀገሬ ከመጣህ ይኸው ቃሌን ሳልመልሰው
ማርያም ምስክር ትሁነኝ ፍፃሜህ አያምርም አንተ ሰው››
ብሎ ተናግሮ ነበር ያን ወራሪ ድል የነሳው፡፡
ያ የሀበሻ ንጉስ ያ ጥቁር ምኒልክ
ሰውን በሰውነቱ የሚያከብር ሰው የመሆን ውሀ ልክ
በዛ የጊዜ ጭጋግ በዛ የዘመን ማታ
"አልገዛም" የማለትን የአፍሪካን አፍ የፈታ፡፡
ስልጣኔን በመፈለግ ዘመን[1] ያሉትን ያስደመመ
ከነጮቹ ቀድሞ ባሪያ ፍንገላን ያስቆመ፡፡
የጥቁር ቀለም ግርማ ሞገስ የአፍሪካ ኩራት ማሳያ
ያለመገዛት ምልክት የነፃ ህዝብ አርአያ፡፡
አንቺ አፍሪካ በጣዩቱ ፀሀይ ወጣልሽ
ማንም በቀለምሽ አይንቅሽም
አድዋ አፈሯ ይባረክ
ጣዩቱ ስሟ ከፍ ይበል
ጥቁረት ውበትሽ እንጂ መዋረጃሽ አይሆንሽም!
ከእንግዲ በቃኝ በይ
ለባርነት አትማግጂ ልጆችሽን
ኢትዮጵያ አድሳዋለችና አድዋ ላይ ገፅታሽን!!!

[1] ጠብቆ ይነበብ፡፡